# የአደጋ መከላከል ፕሮግራም (APP)

በዋሽንግተን ግዛት ውስጥ የሚገኝ እያንዳንዱ አሰሪ በስራ ቦታው ላይ የሚያጋጥሙ የደህንነትና የጤና አደጋዎችን ለመፍታት የጽሁፍ የአደጋ መከላከል ፕሮግራም ማዘጋጀት ይጠበቅበታል።

**የጽሁፍ የአደጋ መከላከል ፕሮግራም በአዋቂዎች ቤተሰብ ማዕከልዎ ውስጥ የስራ ቦታ ላይ ጉዳቶች እና ህመሞችን የሚከላከሉበት ዕቅድ ነው።**







## የአደጋ መከላከል ፕሮግራም ክፍሎች

- ሰራተኞች የመጀመሪያ የስራ ተግባሮቻቸውን በደህንነት ለማከናወን ምን ማወቅ እንዳለባቸው የተመለከተ አጭር የስራ ላይ መግለጫ
- አስፈላጊ የደህንነት ስብሰባዎችን ወይም ኮሚቴን ጨምሮ ስለ ደህንነት እና የጤና ፕሮግራምዎ የተመለከተ ጠቅላላ መግለጫ።
- የስራ ቦታ ላይ ጉዳቶች እንዴት እና መቼ ሪፖርት እንደሚደረጉ።
- ለደህንነት ምቹ ያልሆኑ ሁኔታዎች እና የስራ አሰራሮች እንዴት ሪፖርት እንደሚደረጉ።
- የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ መስጫ ሳጥኖች መገኛ ቦታን ጨምሮ የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ ተቋማት መገኛ ቦታ።
- የግል መከላከያ መሳሪያ እና ሌሎች የደህንነት መሳሪያዎች አጠቃቀምና አያያዝ።
- ከስራ ቦታ እንዴት ደህንነትን ጠብቆ እንደሚወጣ ጨምሮ በአደጋ ጊዜ (ቃጠሎ፣ ርዕደ መሬት፣ ወዘተ) ምን መደረግ እንዳለበት።
- በስራ ቦታ ላይ ጥቅም ላይ የሚውሉ አደገኛ ኬሚካሎች፣ መድሀኒቶች ወይም ንጥረ ነገሮች እንዴት እንደሚለዩ እና በተጋላጭነት ወቅት መወሰድ ያለባቸው የአደጋ ጊዜ እርምጃዎችን የተመለከተ መረጃ።

ለአዋቂዎች ቤተሰብ ማዕከላት በልዩ ሁኔታ የተዘጋጀ መታረም የሚችል የአደጋ መከላከል ፕሮግራም ቴምፕሌት ለማግኘት ወደ https://adultfamilyhomecouncil.org/safety-manual ይግቡ።

Adult Family Home Council OF WASHINGTON STATE
Long-Term Care Foundation of Washington State
PIM SAVVY COMMUNITY OUTREACH
SHIP Grant Program — Safety and Health Investment Projects — Lni.wa.gov/SafetyGrants
Funding and support provided by the Department of Labor & Industries